# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE FOUR: ስሜታዊ ትግሎች

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት MEET IN TOWN TO GO TO SCHOOL**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: አቶ ሙላቱ AND ወ/ሮ ሉሊት HAVE BREAKFAST AT HOME**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 3: ዳንኤል AND ንጉሴ CHAT UP ምህረት IN SCHOOL**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ንጉሴ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 15)**

## SCENE 4: ዳንኤል TALKS TO HIS FATHER አያና OVER INTERNET WEBCAM

- አያና (M, 50)
- ዳንኤል (M, 15)

### 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የአፍሪቃ ወጣቶች በሚያጋጥማቸዉ ፈተና ላይ የሚያዉጠነጥነዉን አዲስ ድራማ ክፍል አራት ይዘን ቀርበናል። ለህይወቴ የትኛዉን መንገድ መምረጥ ይኖርብኛል? ማንንስ ነዉ ማመን ያለብኝ? ለህይወት አስፈላጊዉ ነገርስ ምንድን ነዉ? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በዛሬዉ ጭዉዉት ምህረት፤ ዳንኤል እና ንጉሴ ጥረት ሲያደርጉ እናደምጣለን። በቅድምያ ግን እስካሁን የነበረዉን ሁኔታ በአጭሩ ጠቅለል አድርገን እናሰማችሁ።

በመጀመርያዉ የትምህርት ቀን በቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ንጉሴ እና ዳንኤል በራፕ ሙዚቃ ቅላጼ እየተፎካከሩ ሲያዜሙ አድምጠናል።

2. **ዳንኤል (EP 03, LINE 7):** «የሚባለው ስሜ ዳን፡፡ ያይደለሁ ካንተ ወገን! እቅድ አለኝ የምትል፣ ተነሳ ተናገር ለዳን።፡”

3. **ንጉሴ:** “ ተው ባክህ! ፈጽሞ፣ አይሆንም፣ ስማ ስማ ዳንኤል፣ እኔ የአንተ አድናቂ አይደለሁም፡፡ ስሜ ንጉሴ በትንሽ ውስዋሴ፣ ሽዋጅ ነኝ ነፍሴ ቀልድ አይምሰላችሁ ንጉሴ፣ ቀዉጢ፤ ቀዉጢ፤ የገባው ፍሪኪ! ”

4. **ዳንኤል** “ዋው፣ ምን አይነት አስቂኝ ግጥም ነው!”

ለምህረትም ቢሆን የትምህርት ቤቷ የመጀመሪያ ቀን ምንም የማይመች ነበር፡፡ በክፍሉ ዉስጥ ምህረት ብቸኛዋ የድሀ ቤተሰብ እንደመሆኗ የተወሰኑት ልጆች ቀልደውባታል:

5. **ምህረት (LINE 21):** “ ይቅርታ እዚህ አጠገብሽ መቀመጥ እችላለሁ?”

6. **እየሩስ (LINE 27):** “ ለአንዷት ቆሻሻ፣ ደባደቦ ለባሽ፣ ቅርናታም፣ በባዶ እግሯ የምትሄድ ሴት ልጅ? አታስቢው… …”

እና ዛሬስ፤ ምን ይከሰት ይሆን? ምህረት በክፍሏ ተማሪዎች ተቀባይነትን ታገኝ ይሆን? ወንዶቹስ እርስ በርስ ይስማማሉ? የእነዚህን መልሶች ዛሬ በምናደምጠዉ “ስሜታዊ ትግሎች” በተሰኘዉ የታሪኩ አራተኛ ክፍል ተከታተሉ፡፡ ጭዉዉቱ ምህረት እና አዲሷ ጓደኛዋ ትዕግስት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ከተማ ውስጥ ሲገናኙ ይጀምራል።

## SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት MEET IN TOWN TO GO TO SCHOOL

7. **SFX: STREET ATMO WITH PUBLIC TRANSPORT**

8. **ትዕግስት:** **(Yells out)** ምህረት! ዋው፣ የተለየ ሰው መስለሻል! ማለቴ በጣም አምሮብሻል፡፡ የትምህርት ቤት «ዩኒፎርምሽ»ን የገዛሽው መቼ ነው? አዲሱ የጸጉር አሰራርሽም በጣም አስገራሚና ማራኪ ነው። ሆ ሆ እና ክፍል ውስጥ ያሉትን ወንዶች ሁሉ ልታሳብጃቸው ነው ማለት ነዉ!

9. **ምህረት:** አሀ፣ እባክሽን፣ ትዕግስት፤ አታጋንኚ፡፡ ግን ለአድናቆትሽ አመሰግናለሁ፡፡ **(short pause)** በእዚህኛዉ አውቶቡስ እንሂድ?

10. **SFX: OLD VEHICLE APPROACHING**

11. ትዕግስት: ኡኡ በእዚያ ክርካሳ? (chuckles) እንዴ... ምህረት፣ ከየትኛው ፕላኔት ነው የመጣሽው? ስሚንጂ ምህረት፣ አሁን እኮ የቦንጎ አካዳሚ ተማሪዎች ነን። ዝም ብለን አሮጌ የህዝብ ትራንስፖርት መጠቀም አንችልም። ሰማሽ የምንጓጓዝበት ትራንስፖርት መደብ የለየ፣ ዘናጭ እና ከተቻለም ባለ ሙዚቃ መሆን አለበት።.

12. ምህረት: ትዕግስት፣ ግን በእውነት ያ ሁሉ አስፈላጊ ነው?

13. SFX: PUBLIC TRANSPORT VAN PLAYING LOUD HIP-HOP MUSIC APPROACHES

14. ትዕግስት: ተረጋጊ! ይሄዉልሽ ተመልከች፣ የምንሄድበት አዉቶቡስ ይሄውልሽ እየመጣ ነው። ዝግጁ ነሽ? በይ እንግባ!

15. SFX: VAN DOOR OPENS, ምህረት AND ትዕግስት GET IN. LOUD HIP HOP MUSIC PLAYING

16. ምህረት: (talking loudly because of loud music) ትዕግስት፣ ይሄ አውቶቡስ እኮ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶአል!

17. ትዕግስት: ችግር የለዉም። ሰዎች እስኪወርዱ እንቆማለን። (whispering) ሾፌሩን እና ወያላውን አየሻቸዉ! አያምሩም?.

18. ምህረት: አህ... ምናቸውም አላማምረኝም አባክሽ ። ለእኔ እንደውም ዱርዬ ነዉ የሚመስሉት።.

KW BEGIN

**19. ትዕግስት:** (laughs) ኸረ ቀስ ልጅት!

**20. ምህረት:** ትዕግስት፣ ወያላው የመጓጓዣ ሂሳብ እንድንከፍል እንዴት አልጠየቀንም? እኛን አይት አድርጎ አለፈ እና ከሌሎቹ ገንዘቡን ሰበሰበ.

**KW END**

**21. ትዕግስት:** (cautions) እሽሽሽሽ! ምህረት፣ ወይ የምር ምንም የማታውቂ ነሽ! ወያላው,,, (searching for words) በጣም የቅርብ ጓደኛዬ ነው! (laughs) ብዙ ማወቅ ያለብሽ ይመስለኛል ፡፡ ልክ ከገጠር ቀጥታ ከተማ እንደወረድሽ አይነት ነገር ሆንሽብኝ፡፡ …

**22. ምህረት:** አዎ እንደዛ አይነት ነዉ,,, ማለቴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቴ ከቤታችን ምንም ያህል ሩቅ አልነበረም፤ ውሃ የምቀዳበትም ሆነ እቃ የምንገዛበት ቦታ ከቤታችን ብዙ አይርቅም። አባቴም ቢሆን ብቻዬን ወደ ከተማ እንድመጣ ፈቅዶልኝ አያውቅም.

**23. ትዕግስት:** እና ታድያ ቤትሽ ግን በትክክል የቱ ጋር ነው?

**24. ምህረት:** ታንዲካ!

**25. ትዕግስት:** (shocked) ዉይ! እዚያ ታንዲካ ጎስቋላ መንደርውስጥ ነዉ የምትኖሪዉ?

**26. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: አቶ ሙላቱ AND ወ/ሮ ሉሊት HAVE BREAKFAST AT HOME</u>**

**26. a) ATMO: SLUM DWELLING AMBIABCE, DAYTIME**

**27. SFX፡ አቶ ሙላቱ BLOWING ON HOT PORRIDGE TO COOL IT DOWN**

**28. ወ/ሮ ሉሊት፡** **(jokingly)** አቶ ሙላቱ እፍታህን ብታቆም ይሻላል ኋላ አጥሚትህ እንዳይቀዘቅዝልህ። እናስከዚያ ምን ትሆናለህ?

**29. አቶ ሙላቱ፡** **(sarcastic)** ሀሀሀ… በጣም አስቂኝ። ጥርሴን እንዳመመኝ በደንብ ታውቂያለሽ። ለጥርስ ሀኪም የምከፍለዉ ደግሞ የለኝም። ስለዚህ ምናልባትም ለሰዓታት ማንተክተክ አልነበረብሽም!

**30. ወ/ሮ ሉሊት፡** ምህረት በዝያ የትምህርት ቤት የደንብ ልብሷ/ ስትታይ በጣም ታምራለች፣ አይደል?

**31. አቶ ሙላቱ፡** የደንብ ልብሱን ለበሰችም አልለበሰች ምህረት ቆንጅዬ ናት። ለማማር የደንብ ልብስአያስፈልጋትም።

**32. ወ/ሮ ሉሊት፡** ሴት ልጃችን በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉ ትምህርት ቤቶች አንዱ በመግባቷ በእውነት አልኮራህም?

**33. አቶ ሙላቱ፡** ኩራት? የምን ኩራት? **(bitterly)** የማላውቃት አንዲት ሴት የትምህርት ቤት የደንብ ልብስስለገዛች እና ሴት ልጄን ጸጉር ቤት ስለወሰደቻት ኩራት? ህፃን ልጄን ለማሳደግ ገንዘብ ከየት እንደሚመጣ ሳላውቅ ካረገዘች ሚስቴ ጋር በጠዋት የተንተከተከ አጥሚት ለመጠጣት ስለተገደድኩኝ ኩራት?

**34. ወ/ሮ ሉሊት:** **(calmly)** ሙላቱ፣ ሁሉም ነገር እንደሚሆን እናደርገዋለን። ከአሰሪህ ገንዘብ መበደር ትችላለህ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰው ሁሉ የሚያደርገው እንደእዚያ ነው!

**35. አቶ ሙላቱ:** **(thinking)** ሌላ የተሻለ ሀሳብ አለኝ። ሉሊት፣ መች የምትወልጂ ይመስልሻል?

**36. ወ/ሮ ሉሊት:** በሚቀጥለው ሳምንት ይመስለኛል። ለምን ጠየቅኸኝ?

**37. አቶ ሙላቱ:** **(in thoughts)** ህምምም…ይህንን መናገር ባልፈልግም ልጁን ለሌላ ሰው ወዲያ ብንሰጠው የተሻለ እንደሆነ አስባለሁ።.

**38. TENSION BUILDING MUSIC**

**39. ወ/ሮ ሉሊት:** **(utterly shocked)** አይሆንም፣ አይሆንም፣ ምን ማለትህ ነዉ፣ አይሆንም፣ ፈጽሞ አይሆንም! ሙላቱ፣ ያንን ማድረግ አትችልም! አልፈቅድልህም!

**40. አቶ ሙላቱ:** አፍሽን ዝጊ፣ አንቺ የማትረቢ ምን የማትረባ ሴት ናት!

**41. SFX: HARD SLAP ON FACE**

**KW BEGIN**

**42. ወ/ሮ ሉሊት:** **(screams in pain)** ዉዉዉዉ! አትግደለኝ!

**43. አቶ ሙላቱ:** **(threatening)** ሉሊት፣ ሌላ ቃል እንዳይወጣሽ! ሰማሽኝ? አንዲት ቃል እንኳ!

44. ወ/ሮ ሉሊት: (fearful) አዎ ሰምቼሀለሁ።

45. አቶ ሙላቱ: የእዚህ ቤት አባወራ እኔ ነኝ! ወስኛለሁ! እኔ ህግ አረቃለለሁ አንቺ ደግሞ በህጉ ትገዢያለሽ!

46. ወ/ሮ ሉሊት: (fearful) እሺ..

**KW END**

47. አቶ ሙላቱ: ህጻንዋን የሚንከባከብልን አንድ ሰው እፈልጋለሁ። ሌላ ልጅ ማሳደግ አንችልም። (To ወ/ሮ ሉሊት) ይህ አጥሚት ቀዝቅዟልበዚያ ላይ አይጣፍጥም። እና አሁን ሌላ ነገር ለመጠጣት መዉጣቴ ነዉ!

**48. SFX: IRON SHEET DOOR BEING OPENED AND CLOSED**

**49. SAD, MELANCHOLIC MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ዳንኤል AND ንጉሴ CHAT UP ምህረት IN SCHOOL**

**50. SFX: SCHOOL ATMO FOLLOWED BY BELL RINGING**

**51. SFX: ATMO OF STUDENTS LEAVING CLASSROOM**

52. ትዕግስት: (sigh of relief) ኡፈይ …ደወሉ ከአሁን አሁን በተደወለ እያልኩ ነበር። በመስተመጨረሻ የእረፍት ሰዓት ደረሰ፣ ምህረት! ትምህርቱ ሁሉ ሰልችቶኛል- የባዮሎጂ መግቢያ፣ የፊዚክስ መግቢያ፣ የኬሚስትሪ መግቢያ… ,,, ኤጭ!

53. **ምህረት:** እኔ ግን ደስ የሚል መስሎኝ ነበር። በተለይ ባዮሎጂ- "የህይወት እና ህይወት ያላቸው ነገሮች ጥናት"

54. **ትዕግስት:** ባክሽን፣ ምህረት፣ አቁሚ! ሴት ልጅ በየመሀከሉ እረፍት ያስፈልጋታል።

55. **SFX: MAN WOLF-WHISTLING**

56. **ትዕግስት:** **(seductive tone)** ኦሀ፣ የሆነ ሰውን ትኩረት እንደሳብሽ ይታየኛል። ነግሬሽ አልነበር- ወንዶቹን ሁሉ ጉድ ልታፈይባቸው ነው።

57. **SFX FOOTSTEPS - ዳንኤል APPROACHES**

58. **ዳንኤል:** ይቅርታ፣ ምህረት ላነጋግርሽ እችላለሁ... ለብቻችን.

59. **ምህረት:** **(indifferent)** ለምን ለብቻችንን? እኔ የምደብቅበት ምንም ነገር የለም።

60. **ትዕግስት:** ምህረት፣ እንዲህማ ገገማ አትሁኚ፣ ይግባሽ እንጂ፤ ዳንኤል ብቻሽን ሊያናግርሽ ይፈልጋል።

61. **ምህረት:** አውቃለሁ፣ የፈለገውን ግን እዚህ ፊት ለፊት ሊናገር ይችላል።

62. **ዳንኤል:** **(confused)** እሺ እንድያ ከሆነ--፤ በጣም ቆንጆ እንደሆንሽ ልነግርሽ እፈልጋለሁ እና– **(cut short by ንጉሴ)**

63. **SFX FOOTSTEPS - ንጉሴ APPROACHES**

64. **ንጉሴ:** **(clears throat)** እዚህ ጋር ችግር አለ?

65. ዳንኤል: (annoyed) የምን ችግር? እዚህ ጋር የሚታየኝ ብቸኛ ችግር ቢኖር አንተ ነህ!

66. ትዕግስት: (sarcastic) ኡፒስ፣ ተጨማሪ ችግር። ያዝ አንግዲህ……

67. ምህረት: (confused) ሆሆ…ግድ የለም ንጉሴ፣ ምንም አልሆንኩም። ስላሰብክልኝ አመሰግናለሁ። ትዕግስት ወደ ክፍል እንመለስ።

68. ዳንኤል: ምህረት፣ ወደ ክፍል ልሸኝሽ እችላለሁ? በርግጥ የሚቻል ከሆነ ማለቴ ነዉ ።

69. ንጉሴ: በጣም አሪፍ አንግዲህ እንደ ክፍል አለቃነቴ እኔ ብመልሳት የተሻለ ይመስለኛል። ለአንተ ጥያቄ በግልፅ ፍላጎት አላሳየችም,,,

70. ምህረት: (playing kind) ሁለታችሁንም አመሰግናለሁ። ግን ብቻዬን መሄድ እችላለሁ። ነይ እንጂ ትዕግስት። ወይስ አጃቢ ፈልገሻል? (chuckling)

71. ትዕግስት: (jealous) ማን? እኔ? … አይ፣ አልፈልግም…ማለቴ እኔን ማንም አልጠየቀኝም።

72. ምህረት & ትዕግስት: (chuckle as they leave)

73. **SFX: FOOTSTEPS - ምህረት AND ትዕግስት LEAVING**

74. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ዳንኤል TALKS TO HIS FATHER ኢያና OVER INTERNET WEBCAM</u>**

**75. SFX: ATMO DORM (LIGHT TRAFFIC NOISE FROM OUTSIDE, FAN)**

**76. SFX: INTERNET CALL (Skype) BEING CONNECTED, MOUSE CLICKS**

**77. ኢያና:** ሄሎ ዳንኤል፣ ትሰማኛለህ? አባትህ ኢያና ነኝ።

**78. ዳንኤል:** አዎን አባዬ እሰማሀለሁ፡፡ እዚህ ሀገር የኢንተርኔት ፍጥነቱ በጣም ቀርፋፋ ነው፡፡

**79. ኢያና:** ኧሀ፣ ይሁን፡፡ የኢያና ስርወ መንግስት ወራሽ የውጭ ሀገር ልምምዱ ምን ይመስላል እባክህ ? ንገረኝ እስቲ፡፡

**80. ዳንኤል:** እባክህን አባዬ ይህን ነገር አቁም፡፡ እኛ ስርወ መንግስት አይደለንም፡፡

**81. ኢያና:** አይደለንም? የአባትህን ስም ግን ይዘሀል፣ አይደለም እንዴ? ኢያና የተከበረ እና ገናና ስም ነው፡፡ እዛ ባለህበት በኪሲምባ የእኛን መልካም ዝና እያጎላህ እንደሆን አስባለሁ።

**82. ዳንኤል:** አዎ ልክ ነው አባዬ፡፡.

**83. ኢያና:** ጥሩ፡፡ እና እንዴት ነህ ታድያ?

**84. ዳንኤል:** ሁሉም ነገር መልካም ነው አባዬ፡፡

85. ኢያና: ዌብካምህን/የቪዲዮ መቅረጫዉን/ በመጠቀም ክፍልህን ልታሳየኝ ትችላለህ? የምከፍልበትን ነገር ማየት እፈልጋለሁ።

86. ዳንኤል: አባዬ፣ ይቅርታ፣ አሁን ላሳይህ አልችልም። ክፍሉ አልጸዳም፡.

87. ኢያና: (annoyed) አንተ ሰዉዬ አሁንም ትንሽ እንኳ አልተለወጥክም! እኔ እና እናትህ እዚያ የላክንህ ኃላፊነት እንዴት ሊሰማህ እንደሚችል እንድትማር ነበር!

88. .ዳንኤል: አውቃለሁ። ይህንን ሌላ ጊዜ ልናደርገው እንችላለን? አባዬ። ክፈሉን እንደማሳይህ ቃል እገባልሃለሁ። ግን ዛሬ አይደለም።

89. ኢያና: ይሁን፤ ጥሩ ነው። በግማሽ መንፈቀ ዓመቱ መጥቼ ልጎበኝህ እየተዘጋጀሁ ነው።

90. ዳንኤል: አባዬ፣ አንድ የሆነ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። ገንዘብ አልቆብኛል።

91. ኢያና: (shocked) ከመቼው? ዳንኤል የኪስ ገንዘብ ወደ 1000 የዩኤስ ዶላር ሰጥቼህ ነበር! ምን አረክበት?

92. ዳንኤል: እዚህ ሁሉም ነገር ውድ ነው! አሁን ምንም ገንዘብ የለኝም።

93. ኢያና: ህምምም... እሺ ይሁን። ግን የገንዘብ አያያዙን መልመድ አለብህ፣ ዳንኤል። ቅዳሜ ጥቂት ገንዘብ እልክልሀለሁ። ነጻ የምሆነው በዚያ ቀን ብቻ ነው።

**KW BEGIN**

**94. ዳንኤል:** የሆነ ሰው ነገ እንዲልክልኝ ማድረግ አትችልም?

**95. አያና:** **(strict)** ሄሄሄይ። ቅዳሜ ብያለሁ። አታስጨንቀኝ እንግዲህ ። እና ታድያ ልትነግረኝ የፈለከው ይህ ብቻ ነው? ተጨማሪ ገንዘብ እንድልክልህ?

**96. ዳንኤል:** አዎ…ይኸዉ ብቻ ነዉ,,,

**97. አያና:** እና እናትህ እንዴት እንደሆነች ጤንነትዋን እንኳ ማወቅ አትፈልግም? የቤተሰቡስ ንግድ እዴት እንደሆነስ አትጠይቅም?

**98. ዳንኤል:** **(ashamed)** በርግጥ ፈልጌ ነበር። እማዬ እንዴት ናት?

**99. አያና:** ያው እንደሁልጊዜው በፈጣሪዋ እንደተመሰጠች ነው። ሌላ ቦታ ከምታሳልፈው ጊዜ ይልቅ በቤተክሲያን የምታሳልፈው የሚበልጥ ይመስለኛል። ግን ደህና ነች።

**KW END**

**100.ዳንኤል:** **(short pause, bored)** እና ስራ እንዴት ነው? እንደተለመደው አሪፍ ነው?

**101.አያና:** ዳንኤል እኔ ስሞት ንግዱን የምትረከበው አንተ ነህ። ስለዚህ ከአሁኑ ልታስብበት እና ኃላፊነት ሊሰማህ ያስፈልጋል።

**102.ዳንኤል:** **(weary)** አባዬ በዚህ ጉዳይ ላይ ሺህ ጊዜ ነው የተነጋገርነው! እኔ ለማዕድን ስራ ፍላጎት የለኝም ብዬሃለሁ

**103.ኢያና:** አዎ እና እኔም ሚሊየን ጊዜ ነግሬሀለሁ፣ እድልህን ማምለጥ አት።

**104.SFX: NOISE, INTERNET CALL DISCONNECTED**

**105.ዳንኤል:** ሃሎ? ሃሎ?? አባዬ? አይሰማኝም? የእኔ ይሰማሃል? **(ironically)**

መጥፎ አጋጣሚ,,,,

**106.MUSIC INTERLUDE**

**107.<u>OUTRO - NARRATOR :</u>**

ዳንኤል ከአባቱ ጋር የሚያደርገው ንግግር በአጭሩ በመቋረጡ እጅግ የተቆጨ አይመስልም። ከቤቱ በጣም የራቀ ቢሆንም የአባቱን ሀብትግን መዉረስ እንደማይፈልግ ተሰምቶታል። ምህረትም ከገጠማት አዲስ ሁኔታ ጋር እየታገለች ነዉ። በአንድ ጊዜ ሁለት አድናቂዎቿን እንዴት ታስተናግድ ይሆን? መልሱን በሚቀጥለዉ  በምናቀርበዉ “መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ” በተሰኘው የበማድመጥ መማር ድራማ አምስተኛ ክፍል ላይ ያድምጡ። dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ-ገጻችንን እንዲሁም የፌስቡክ ገፃችንንም ይጎብኙ። ለዛሬ እዚህ ላይ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።